# ሌላ ዋና ተንከባካቢ (OPC) ቅጽ – 2024-25 የትምህር አመት

የሚመዘገበው ተማሪ በ “ሌላ ዋና ተንከባካቢ” እንክብካቤ ስር መሆኑን ለማረጋገጥ **ይህን ቅጽ ይጠቀሙ**። የትምህርት ቤቱ ሀላፊዎች ይህን ቅጽ መሰብሰብ ያለባቸው ተማሪውን የሚያስመዘግበው ሰው የተማሪው ወላጅ፣ ህጋዊ ሞግዚት ወይም በፍርድ ቤት የተሾመ አሳዳጊ ካልሆነ እና ወላጁ፣ አሳዳጊው፣ ወይም ሞግዚቱ በከባድ የቤተሰብ ችግር ምክንያት የሚፈለገውን እንክብካቤ እና ድጋፍ መስጠት የማይችል ከሆነ ብቻ ነው።

## ደረጃ አንድ፣ OPC መሆንዎን መለየት።

“ሌላ ዋና ተንከባካቢ” ማለት ከወላጅ፣ በፍርድ ቤት ከተሾመ አሳዳጊ ወይም ሞግዚት ውጭ ከራሱ ጋር ለሚኖር እና ወላጁ፣ አሳዳጊው፣ ወይም ሞግዚቱ በከባድ የቤተሰብ ችግር ምክንያት እንክብካቤ እና ድጋፍ ሊሰጠው ላልቻለ ልጅ እንክብካቤ እና ድጋፍ የሚሰጥ ዋና ተንከባካቢ ማለት ነው። OPC በDC (ዲሲ) የኗሪነት ማረጋገጫ ቅጽ ላይ እንደሚፈለገው፣ የእሱን/ የሷን “ሌላ ዋና ተንከባካቢ” ሁኔታ ከማረጋገጥ በተጨማሪ የDC ኗሪነታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። የእንክብካቤ ወይም የቁጥጥር እና ዋና ድጋፍ ትርጉምን ለማወቅ ግልባጩን ይመልከቱ።

## ደረጃ ሁለት፣ ስለሌላ ዋና ተንከባካቢ ሁኔታ መረጃ ያቅርቡ።

| | | |
|---|---|---|
| **የተማሪ የመጠሪያ ስም፣** | **የተማሪ የአያት ስም፣** | |
| OPC **የመጠርያ ስም፣** | OPC **የአያት ስም፣** | |
| OPC **አድራሻ፣** | | **አፓርታማ፣** |
| **ከተማ፣** | **ክልል፣** | **ዚፕ፣** |
| **ከተመዝጋቢው ተማሪ ጋር ግንኙነት፣** | **ተማሪው ከሌላ ዋና ተንከባካቢ ጋር መኖር የጀመረበት ቀን፣** | |

**የ**OPC **ሁኔታ ማረጋገጥ (የሚመለከተውን ሁሉንም ይምረጡ)፣**

☐ እኔ ለተመዝጋቢው ተማሪ እንክብካቤ ወይም ቁጥጥር እሰጣለሁ
☐ እኔ ለተመዝጋቢው ተማሪ አብዛኛውን ድጋፍ እሰጣለሁ
☐ ተመዝጋቢው ተማሪ ከኔ ጋር ይኖራል፣ ሌላ ዋና ተንከባካቢ

## ደረጃ ሶስት፣ ስለወላጅ/ህጋዊ ሞግዚት መረጃ ያቅርቡ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የወላጅ/ህጋዊ ሞግዚት ሙሉ ስም፣** | | | |
| **የወላጅ/ ህጋዊ ሞግዚት አድራሻ፣** | | | |
| **ከተማ፣** | **ክልል፣** | **ዚፕ፣** | **ስልክ፣** |

**ወላጅ ወይም ህጋዊ ሞግዚት በሚከተሉት ከባድ የቤተሰብ ችግር ምክንያት( የሚመለከተውን ማንኛውንም ይምረጡ) ዋና እንክብካቤ እና አብዛኛውን ድጋፍ ሊሰጡ አልቻሉም ፣**

☐ እሱ/እሷ በሚሊታሪ ምድብ ላይ ናቸው
☐ እሱ/እሷ በከባድ ህመም ይሰቃያሉ
☐ እሱ/እሷ ሞተዋል
☐ እሱ/ሷመኖሪያነት ማጣት እያጋጠመው/ማት ነው
☐ እሱ/እሷ ታስረዋል
☐ እሱ/እሷ ልጁን ባለመንከባከብ እና /ወይም ጥቃት በማድረሳቸው ምክንያት አብረው አይኖሩም
☐ እሱ/እሷ ልጁን ጥለውታል
☐ እሱ/ሷ ከሁገር በመባረር ምክንያት አይገኝም/አትገኝም

## ደረጃ አራት ፣ የOPC ሁኔታ ማረጋገጫ።

ከታች በመፈረም፣ እኔ ሌላ ተንከባካቢ መሆኔን እና ወላጁ፣ አሳዳጊው፣ ወይም ሞግዚቱ **በከባድ የቤተሰብ ችግር** ምክንያት የሚፈለገውን እንክብካቤ እና ድጋፍ መስጠት እንዳልቻለ እምላለሁ እና አረጋግጣለሁ። እኔ በተጨማሪ ሁሉንም በDC(ዲሲ) የኗሪነት ማረጋገጫ ቅጽ በ “ደረጃ ሶስት የኗሪነት ማረጋገጫ መስፈርቶችን” ላይ የተቀመጡት ሁልም አንቀጾች እዚህ መካተታቸውን እቀበላለሁ።

**ሌላ ዋና ተንከባካቢ እዚህ ይፈርሙ፥**____________________________ **ቀን፥** ____________________

## ለትምህርት ቤት ሀላፊ አገልግሎት ብቻ

ትምህርት ቤቱ ሌላ ዋና ተንከባካቢ ሁኔታ እንዳሎት እንዲያረጋግጥ ከታች ያለውን ስፍራ ይሙሉ።

እኔ ከላይ በተገለጸው መሰረት የOPC ሁኔታን መርምርያለሁ እና OPC ሁሉንም ሶስቱንም መስፈርቶች ያሟላሉ እና ወላጁ ወይም ህጋዊ ሞግዚቱ በከባድ የቤተሰብ ችግር ምክንያት ዋና እንክብካቤ እና አብዛኛውን ድጋፍ መስጠት አይችሉም። በተጨማሪ፣ ከላይ የተለየው OPC የ OPC ሁኔታዎችን ለማረጋገጥ ከሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ አንዱን አቅርቧል፣

☐ በቃለ መሀላ የሆነ መግለጫ
☐ ከቀደመው የትምህርት አመት ሪከርዶች
☐ ክትባቶች ወይም የሜዲካል ሪከርዶች
☐ ጊዜው ያላለፈበት ኦፊሺያል ሰነድ ከፌደራል መንግስት ወይም ከ Columbia (ኮሎምቢያ) ግዛት መንግስት
☐ ለሌላ ዋና ተንከባካቢ ማረጋገጫ

እኔ የቀረቡትን ሁሉንም ሰነዶች መመርመሬን እና ከላይ የቀረበው መረጃ በኔ እውቀት፣ መረጃ እና እምነት መሰረት እውነት መሆኑን፣ ይህ ባይሆን ግን ሀሰተኛ ነገር በመግለጽ ቅጣት የሚከተለኝ መሆኑን በማወቅ አረጋግጣለሁ። እኔ በተጨማሪ ሁሉም የዚህ ቅጽ ደጋፊ ሰነዶች በትምህርት ቤቱ የሚያዙ እና ሲጠይቁ ለ OSSE ፣ የውጭ ኦዲተሮች፣ እና ሌሎች ኤጀንሲዎች፣ የ DC (ዲሲ) ጠቅላይ መርማሪ ቢሮ እና የ DC (ዲሲ) ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ቢሮ እንደሚሰጥ አረጋግጣለሁ።

**የትምህርት ቤት ሀላፊ ስም (ይጻፉ)፣** __________________________ **ፊርማ፣** ________________ **ቀን፣** ______________

| OPC የሌላ ዋና ተንከባካቢ ሁኔታውን ለማረጋገጥ ከታች ከተለዩት ሰነዶች አንዱን ማቅረብ አለባቸው። | |
|---|---|
| **ዘዴዎች** | • እሱ /እሷ የተማሪው ዋና ተንከባካቢ መሆናቸውን የሚያመለክት **የተሞላ እና የተፈረመ በቃለመሀላ የሆነ የጽሁፍ መግለጫ**።<br>• ተማሪው በተንከባካቢው እንክብካቤ ስር መሆኑን የሚያመለክት የተፈረመ የሪፖርት ካርድን ጨምሮ **ያለፈ የትምህርት አመት ሪከርዶች** ።<br>• ተማሪው በተንከባካቢው እንክብካቤ ስር መሆኑን የሚያመለክት ትምህርት ቤቱ የኗሪነት ሰነዱን ከመመርመሩ በፊት ያሉትን ያለፉት የ12 ወራት **የክትባት ወይም የሜዲካል ሪከርዶች**<br>• **ጊዜው ያላለፈበት ኦ ፊሺያል የፌደራል መንግስት ወይም የ Columbia (ኮሎምቢያ) ግዛት መንግስት** ሰነድ ትምህርት ቤቱ የኗሪነት ሰነዱን ከመመርመሩ በፊት ባሉት 12 ወራት ውስጥ የተሰጠ፣ ተንከባካቢው ተማሪውን በመወከል የህዝብ ወይም የሜዲካል ጥቅማጥቅሞችን መቀበሉን የሚያመለክት ፣ ተጨማሪ የዋስትና ገቢ አመታዊ ጥቅማጥቅሞችን ማስታወቂያ ወይም የችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ የገንዘብ እርዳታ (TANF) የገቢ ማረጋገጫ ማስታወቂያ ወይም የድጋሚ ማረጋገጫ ፍቃድ ደብዳቤ<br>    • **በህጋዊ፣ ሜዲካል ወይም ማህበራዊ አገልግሎት ባለሞያ የተሞላ እና የተፈረመ የOPC ማረጋገጫ** ይህም ተንከባካቢው ለተማሪው ያለውን አስፈላጊነት የሚያረጋግጥ እና ትምህርት ቤቱ የኗሪነት ሰነዱን ከመምርመሩ በፊት ባሉት ባለፉት 12 ወራት ውስጥ የተሰጠ መሆን አለበት። |

## እኔ ሌላ ዋና ተንከባካቢ ነኝ?

5-A DCMR § 5099 እንደሚገልጸው ሌላ ዋና ተንከባካቢ (OPC) ማለት ከተመዝጋቢው ተማሪ ወላጅ ወይም በፍርድ ቤት የተሾመ አሳዳጊ ወይም ሞግዚት ውጪ የሆነ ሰው ማለት ነው። ተመዝጋቢው ተማሪ ከOPC ጋር *መኖር* አለበት እና OPC *ለተማሪው መመርያ፣ ቀለብ፣ የአካል እንክብካቤ እና ድጋፍ መስጠት አለበት*። በተጨማሪም፣ **የተማሪው ወላጆች፣ ሞግዚቶች፣ ወይም አሳዳጊዎች በከባድ የቤተሰብ ችግር ምክንያት ለተማሪው ዋና እንክብካቤ እና አብዛኛውን ድጋፍ ሊሰጡ አይችሉም።** እርስዎ መመርያ፣ ቀለብ፣ እና አካላዊ እንክብካቤ የማይሰጡ ከሆኑንም እና የተማሪው ወላጆች፣ ሞግዚቶች፣ ወይም አሳዳጊዎች ከባድ የቤተሰብ ችግር ከሌለባቸው፣ እርስዎ ለOPC ብቁ አይደሉም። እርስዎ ከታች ባለው ሰንጠረዥ ያሉትን ያቀርባሉ?

| | |
|---|---|
| **ድጋፍ** | OPC ለልጁ መኖርያ የገንዘብ ወጪ ለማድረግ *ዋና ሃላፊነት* ሲወስድ። |
| **መመርያ** | OPC በየእለቱ ለልጁ እድገት በሃላፊነት ሲሳተፍ፣<br>• የልጁን የትምህርት ቤት ኮንፈረንሶች ላይ ሲሳተፍ<br>• ልጁን ስነምግባር ሲያስይዝ<br>• የልጁን ደህነነት አስመልክቶ በውሳኔ ሰጪነት ሲሳተፍ።<br>• በልጁ ከትምህርት ቤት ውጪ በሆኑ እንቅስቃሴዎች ሲሳተፍ |
| **ቀለብ** | OPC መሰረታዊ ነገሮችን ሲያቀርብ፣<br>• ምግብ<br>• ልብስ<br>• መጠለያ |
| **የአካል እንክብካቤ** | OPC በልጁ የእለትተለት ህይወት የሚያስፈልጉትን ተግባሮችን በመፈጸም ለልጁ የማያቋርጥ እንክብካቤ ሲሰጥ፣<br>• ገላ ማጠብ<br>• መመገብ<br>• ማልበስ<br>• ልጁ የሜዲካል ክትትል እንደሚያገኝ ማረጋገጥ<br>• ምግቦችን ማዘጋጀት<br>• የልጁን እንቅስቃሴዎች መከታተል<br>• ሌሎች የአካል እንክብካቤ ፍላጎቶች ጋር መርዳት |